# የአዲሲቱ ኢትዮጵያ

የሕዝባዊ፣ የብልጽግና፣ የአስተዳደር

ስርዐቶች መመስረቻ

አንድ ዕቅድ

## የፖለቲካ መደቦች መዋቅር

**በዘውገ ፋንታ**

## የሕዝባዊ፣ ብልጽግና፣ አስተዳደር ስርዐቶች መመስረቻ

## አንድ ዕቅድ

## ክፍል አንድ

*መግቢያ*

በዚህ የቀረበው፣ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ፣ ብልጽግና፣ አስተዳደር ስርዐቶች መመስረቻ ዕቅድ ነው። ይኽ ጸሐፊ፣ በዚህ ዕቅድ ላይ ብዙ በማሰላሰል ያዋቀረውን ጽንሰ-ሃሳብ አቅርቧል። የዕቅድ ዋና አላማ፣ ውጥንቅጥ እና አስቸጋሪ ሆኖ የቆየውን፣ አሁን ደግሞ እጅግ ተፋፍሞ የሚገኘውን የክምችት (የጎሳ) ኋላ-ቀር፣ ዘመን የተላለፈበት አስተሳሰብ አስወግዶ፣ በምትኩ ዘለቄታ ያለውን ሀገር መመስረቻ እና ገንቢ ስርዐትን ለማቅረብ ነው።

ከብዙ አሰቃቂ መከራ በኋላ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የነቃ ትውልድ እና ብልህ መሪዎችን አፍርቷል ወይም እንደሚባለው፣ አምላክ አዘጋጅቶ ሰጥቶታል። ይህ ዕቅድ የዘመኑ ብልህ ትውልድ እና ምርጥ መሪዎች አማካይነት፣ ኢትዮጵያን በሰላም ጎዳና ከድህነት ወደ ብልጽግና ለማሸጋገር እንዲረዳ ታልሞ የቀረበ ነው። ዕቅዱ ሰፊ ለውጥን ስለሚያመጣ የሚከብድ ይመስላል። በዚህ ንቁ እና ብልህ ትውልድ እና ቆራጥ መሪዎች አማካይነት የማይቻል አይሆንም። እጅግ ሰልጥኗል የሚባለው የውጪ አለም ሕዝብ ይህንን መሳይ ዕቅድ በስራ ለማወል፣ ባህሉ እና ባሕሪው እንዲሁም የተጓዘበት ታሪክ እንቅፋት ሰለሚሆኑበት አይችልም። አሁን ያሉበት ስር የሰደደ የኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ሕዝባዊ ስልቶች እና ፍልስፍናቸው የሚቀለበሱ አይደሉም። ይህ በመሆኑ፣ በየቦታው አዲስ ስልጣኔ እየተነሳ እና እየጠፋ ቆይቷል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ቀዳማዊ ስልጣኔውን ፈጽሞ ሳያጠፋ በተንጨላጨለ ጥበብ ቢሆንም ታሪኩን ጠብቆ የቆየ መሆኑ የሚታይ ነው። አሁን ደግሞ በላቀ መልክ አዲስ ታሪክ ሲጀምር፣ አሁን ያለው ሁኔታ ምቹ ያረገዋል። ስለዚህ ይህ ዕቅድ ኢትዮጵያ ካለችበት ፈታኝ ችግር ወደ ሰላም እና ብልጽግና ጎዳና የሚያስገባት ይሆናል። በዚህ ዕቅድ የማይፈወስ፣ የማይነጻ እና የማያድግ ማንም ኢትዮጵያዊ አይኖርም።

ባዲስ መንፈስ እና በአዲስ ባህሪ የተነሳው ትውልድ፣ ወደ አዲስ ዘመን ለመግባት የሚጓጓ ብቻ ሳይሆን፣ ቆርጦ የተነሳ መሆኑ እየታየ ነው። ከፍተኛ ሀገራዊ፣ አህጉራዊ እና አለምታዊ ስሜት ይንጸባረቅበታል። ለሀገሬ የሚለው ለራሱ ጥቅም እና ኩራት እንደሆነ ተገንዝቧል። ይህን ዕቅድ የኢትዩጵያ ሕዝብ በግብር ሲያውለው ምናልባት ለአለም አዲስ ምዕራፍ የሚያበረክት ይሆናል። ኢትዮጵያ በአለም የመጀመሪያ ሪፐብሊክ ነበረች ተብሏል። አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ ሌላ ፍርስፍና መጀመሯ እንዲሁ ታሪካዊ ድርጊት መደጋገሟን ያስመሰክራል። ኢትዮጵያ አለምን በብዙ ጥበብ ዘርፎች እያስናቀች ቆይታለች። በቴወድሮስ፣ ዮሐንስ፣ በምንሊክ ጌቶች የተሰሩት

ታሪኮች እና በታላቁ አፄ ኃይለሥላሴ ያንጸባረቀችው ኢትዮጵያ፣ በያንዳንዱ ሰው ስሟ አለምን ያስናቀው የነ አበበ በቂላ፣ ማሞ ወልዴ የተጀመረው ' አረንጓዴ ጎርፍ፣ አሁን ደግሞ፣ በነ ሮቤል ባምላክ የሚታየው ኢትዮጵያን በልዩ ዘመን የሚያስቀምጣት ይኖናል።

ይህ ዕቅድ የማናቸውንም ኢትዮጵያዊ ዘርፍ ወይም ጎሳ ባህልና ታሪክ የሚያወድቅ ወይም የሚያሳንስ አይደለም። አንዱ ዘርፍ ሌላውን እንዲውጥ አያደርግም። የብዙ ክምችት ማንኛውንም ግለሰብ በዝቅተኛ እና በአነስተኛ መልክ ተጽእኖ እንዳያደርግ ይጠበቃል። በጎሳዎች መካከል፣ በማናቸውም ረገድ መበላለጥ አይኖርም። ጎሳዎች የመንፈስ ሰፊ አድማስ እንጂ የእግር ክልል የላቸውም። የብዙው ሰው መብት በግለሰብ መብት የሚመሰረት እንጂ፣ የግለሰቡ መብት በብዙ ሰው መብት ውስጥ የሚዋቀር አይሆንም። ሰፌው ሕዝባዊ፣ ብልጽግና፣ እና አስተዳደር ስርዓት መመስረቻ በዚህ መሰረታዊ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ ይሆናል። የፖለቲካ መደቦች መዋቅርም በዚሁ ፍልስፍና ላይ የተጸነሰሰ ሲሆን፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መደቦች አርማ ይሆናሉ። ኢትዮጵያ ከዘውድ አስተዳደር ወጥታለች። የተተከሉት የውጭ አስተዳደር ፍልስፍናዎች፣ ኮሚንዝም፣ ሶሽያሊዝም፣ የወያኔ ጤናቢስ ህልውና ኢትዮጵያን ሳይጠቅሙ ትውልድን አልባ አድርገው አልፈዋል። ከነዚያ የጥፋት ጎዳናዎች የተገኘው ትምሕርት ብዙ ነው።

ኢትዮጵያን አገላብጦ ያያትና ተንትኖ የሚያውቃት የራሷ ወገን መሆኑ አያጠራጥርም። ይህ ዕቅድ በዚሁ አንጻር የሚታይ መሆን አለበት። ስለሆነም፣ ጽንሰ-ዕቅዱ የሕዝቡ ታሪክና መሰረታዊ ፍልስፍናዎችን አጣምሮ የያዘ ነው። ከዘመኑ የስልጣኔ አስተሳሰብ ጋርም እንዲዋኹዱ ተደርጓል።

## ክፍል ሁለት

**የዕኩልነት ግባቶች** ______________________________

ብልጽግና ያለሰላም፣ ሰላም ያለ-አንድነት አይመጣም። አንድነት ደግሞ፣ እኩል መብት በማይጠበቅ አስተዳደር ውስጥ ሊኖር አይችልም። እኩል መብት በማናቸውም አንድ ኃይል የሚለገስ ስጦታ አይደለም። ይህ ስህተት በቅርቡ ታሪክ ተፈጽሟል። ታሪክ ማስተማርያ ምሳሌ ይሆናል። በሕዝብ የተዋቀረ የአስተዳደር ፍልስፍና እና ጥበብ በምግባር የሚውለው፣ በሰፊ ዜጋ ተሳትፎ አማካይነት ነው። የአንድ ግለሰብ መብት፣ የብዙውን (ክምችት) ሰው መብት ያበስራል። የብዙ ሰው መብት ግን ያንዱን ሰው መብት ሊነፍግ ይችላል። ስለዚህ፣ ያንድ ሰው መብቶች በህግ ሊደነገጉ ሲችሉ፣ የክምችቱ (የብዙ ሰው) መብቶች የነጠላ ዜጋ መብቶች ጋር የሚጋጩ እና የሚጻረሩ ስለሚሆኑ በህግ የሚደነገጉ አይደሉም። አንድ ሰው የግል መብቱን ይዞ በሀገሪቱ ውስጥ የትም ግዛት ውስጥ ሊኖር፣ ሊሸቅጥ ወይም ሊገዝ እንዲችል መብቱ በህግ የተጠበቀ ይሆናል። የክምችት መብቶች ከግለሰቡ መሰረታዊ መብቶች የሚልቁ መሆን አይችሉም። የሚያደርጋቸው ስልጣን ሊደነገግ አይችልም። አንድ ሀገር የያንዳንዱን ዜጋ ዕኩል መብት ለማብሰር ከጎሳ ወይም ክምችት መብቶች አስተሳሰብ መራቅ አለበት። ቀደም ብሎ

እንደተገለጸው፣ ሕገ-መንግሥቱ ሲወጠን፣ በጎሳ ወይም በክምችት መልክ የሚደለደል እና የሚዋቀር አይሆንም። ይህ ፍልስፍና የረቀቀ ጥበብ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባህሪ ለዲሞክራሲያዊ ለውጥ እጅግ አስቸጋሪ አይደለም። ከሽፍ እና ወድሞ ያለፈው የከፋ መንግሥት ስርዐት የሕዝብን ህልውና በክሎ ስለሄደ፣ በዚያ የተመረዙ ብዙ ግለሰብ እና ክምችቶች በዚህ ለውጥ ዘመንም ብቅ እያሉ እንቅፋት ለመሆን ይሞክሩ ይሆናል። እነሱን ለማቃናት እና የመላውን ሕዝብ መንፈስ እንዲጋሩ ለማድረግ ብዙ ውጣ ውረድ ይኖራል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ችግር አልፎ፣ በሀገሩ ሰላም እንዲሰፍን ያረጋል። ፍጥረት የለገሰውን የምድር ጸጋ ለራሱ እንዲሁም ለትውልዱ እንዲሆን የሚጀምረውን ሰፊ ልማት የሚጻረር እያደር ይመነምናል።

## ክፍል ሶስት

### ያገር ቅርሶች

ኢትዮጵያ ፍጥረት ሰፊ ጸጋ ከለገሰቻቸው ምድሮች አንዷ ናት። ብዙ የተፈጥሮ ውበትና ጸጋ በምድሯ ውስጥ እና ውጭ የሞሉ ናቸው። ስለዚህም ለብልጽግና ያላት አቋም ወደር የሌለው ነው። ኢትዮጵያ ለብዙ ዘመናት በውጪ ዓለም በብርቅና በአድናቶት እየታየች የቆየች ጥንታዊ ሀገር ናት። የወገኖቿ ውብ እና ድንቅ የሆኑ ባህሎች ልዩ ሞገስና ክብር ያጎናጸፏት ናቸው። በዘመናችን የታየው የጦርነት እና የርሀብ ገጿ ዓለምን ቢያሸብርም፤ በየአህጉሩ በተበታተኑት ወገኖቿ ላይ እየደረሰ ያለው ግፍ እና ውርደት፣ የሕዝቧን ክብርና ታሪክ የሚፍቀው አይሆንም። ለዚህ ያበቁት አንድ፣ የሕዝቡ ተላላነት እና የክምችቶች ራስን ወዳድነት ሲሆን፣ በተጨማሪም ትውልድ በማያዋጣ ቅንጦት መሰማራቱ ነበር። ሁለተኛ፣ የውጪ ሀብት አዳኝ ራሱን ወዳድ ባዕድ፣ ጊዜ ተመቻችቶለት ወይም ጊዜ ጠብቆ፣ ማበጣበጡን እና ግጭትን ለማፋፋም ዕድል በማገኘቱ ነው። እነዚህ ደግሞ ጸረ-አንድነት ናቸው። ምክንያቱም፣ ብዙ ጥቅም የሚያገኙት ከጥቃቅኖቹ ደካማ ግዛቶች እንጂ ከግዙፏ ኃያሏ ኢትዮጵያ አይደለም። "ኢትዮጵያ አትፈርስም" የጠ/ም ዶ/ር አቢይ ምሐላ ነው። ከዚህ ካለንበት ዘመን ጀምሮ፣ ኢትዮጵይ በሕዝቧ ብልህነት እና ጠንካራነቱ አለምን የሚያስንቅበት ወቅት ይመጣል። ይህ እንዲሆን፣ ባስቸኳይ ያለብንን ሰፊ ምግባር መጀመር ይገባናል። የኢትዮጵያ ወጣት እና ሽማግሌ ስደትን የሚመርጥበት ግፍ ዘመን አብቅቷል። በውጪ ያለው ወገንም፣ ግፍና በደል በዝቶበትና አንገፍግፎት ወደ ሀገሩ ጅር ብሎ ለመመለስ ወር እየጠበቀ ነው። ይህ ሲሆን፣ ይዞ የሚመጣው የዕውቀት ክምችት፥ ጉልበት፣ ፍላጎትን እና ስሜት፣ የገንዘቡ ኃይል በግምት የኢትዮጵያን የአሥር አመት እርምጃ አፋጥኖ በስምንት (?) ከበለጠም የስድስት (?) አመት ለውጥ ያረገዋል!

ኢትዮጵያ አለም ባወቀውና ባጸደቀው ግዛቷ ድንበሮቿን ባላት ኃይል ትጠብቃለች። ሰብዓዊና ዓለም-አቀፍ በሆነው ጉዳይ የሚገባትን አስተዋጽዖ ለአለም ታበረክታለች። ለሷም የሚገባውን መጠየቅና መቀበል ይገባታል። የዜጎቿ መብትና ክብር እንዳይደፈር፣ በግዛቷ ውስጥ ሰላም እንዳይደፈርስ፣ ጸጥታ እንዲከበር ማድረግ ግዴታዋ ነው። ኢትዮጵያ ከማንም ሀገር እና ሕዝብ

ይበልጥ፣ ሶስቱን ታላላቅ ኃይማኖቶች ቤታቸው እንዲሆን አድርጋለች። ይኽም አስከብሯታል። ጥንታዊ ታሪኳ እና የዜጎቿ የተለያዩ ባህሎች እና ቋንቋዎች እንዲከበሩ፣ እንዲጠበቁ እና እንዲዳብሩ የደረገች ሀገር ናት። የሰለጠነው ወገን ይህን ለማድረግ፣ ህጉ ውቅያኖስ ነው። ህግ - አስከባሪው ብዛቱ ጫካ ነው። ኢትዮጵያኖች ህግ አስከባሪዎች ራሳቸው። የሌባው እና አዋኪው ሰው ፍርድ ከዛቸው ከመንገዱ ዳር ወይም መሐል ! ይህ የሕዝብ ባህሪ መንግሥት እንዳይኮልሽ፣ ገንዘብ እንዳያባክን፣ ትውልድ በእስር እንዳይበሰብስ፣ ስራ - ቢስ እንዳይሆን አድርጓል።

## ክፍል አራት

### የህገር ሕልውና____________________________________________

የአለም ሕዝብ ብልጽግናውን ከፍ እያረገ ይገኛል። የአለም የተፈጥሮ የምድር ሀብት እየተንጨላጨላ ስለሄደ፣ የሰው ጉልበት እና የተፈጥሮ ሀብት በብዛት ካለው አፍሪካ እና በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ካለው ሀገር የጋራ ብልጽግና የሚሹት ሀገሮች ብዙ ናቸው። የአንድ ሀገር የብልጽግና ጥፋት እና እንቅፋት እየደረሰበት ያለው አንዱ ዋናው ምክንያት፣ የጋራ ልማት በሆነው ተስቦ ነው። መጥፎ አስተዳደር ከሚፈጽመው ብዙ የሀገር በደል አንዱ እና ዋናው በዚህ መስክ የሚካሄደው የተዛባ አሰራር ነው። ዋናው የሙስና ልምድ ሀገሪቱን አቆርቁዟል።

ዲሞክራሲ ህብረተሰብን ለመገንባት እንጂ ለማፍረስ የሚያገለግል ጥበብ አይደለም። በአንድ ወረዳ ወይም አውራጃ የሚገኝ የኢትዮጵያ ወገን፣ ከቀረው ሰፊ ወገኑ ተገፍቶ ወይም ተገዶ እንዲገነጠል እና ከሚገባው ሰፊ ጸጋ እና ጥቅም እንዳይነፈግ የዲሞክራሲያዊ መብቱ ይከላከልለታል። በዚሁ አንጻር፣ በአንድ ክፍለ ግዛት የሚገኝ ሕዝብ ከተዋኸደው ሰፊ ሕብረተሰብ አካል እንዳይገነጠል የመላው ሕዝብ መብት ያግደዋል። ይህ ዕቅድ የመገንጠል መብትን ከፍልስፍናው ውስጥ አይጨምርም። ለመገንጠል የገባ የለም፣ የገባም መውጫ በር አልተሰራለትም። ሀገር ሲፈርስ በመገነጣጠል ነው። መንግሥት ስራው አንድነትን መጠበቅ ነው።

## ክፍል አምስት

### ወረዳ፣ አውራጃ፣ ጠቅላይ አስተዳደር/እስቴት ________________________________

ኢትዮጵያን በአስተዳደር እና በፖለቲካ ሙሉ ቅርጽ የሚሰጧት ወረዳወች ናቸው። ብዙ ወረዳወች በምድረልሳን አቀማመጣቸው፣ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር አዋሳኝ ይሆናሉ። ይህ ማለት፣ ወረዳወች ለወረራ እና ለዝርፊያ ጥቃትና ጉዳት የተጋለጡ ናቸው። መንግሥት ወሰንን እና ወገንን ለመጠበቅ የማያወላውል ዕርምጃ እንዲወስድ ይገደዳል። በጠረፍ ያለው የወረዳ ሰው ከውስጥ እንዳለው ወገን ተዝናንቶ እንዲኖር፣ መንግሥት በቅድሚያ በወሰን የሚገኙትን ወረዳወች በቀለበት መንገድ ማገናኘት አለበት። ይህ ለጥበቃ ብቻ ሳይሆን ለንግድም ይመቻል።

አንድ አውራጃ ብዙ ወረዳወችን የሚያቅፍ ቢሆንም፣ አንድ ወረዳ ለኗሪው ጠቃሚ ከሆነ ከሌላው ጎረቤት አውራጃ ጋር መጣመሩ ማንንም የሚጎዳ ሆኖ መታየት የለበትም። የአንድ ወረዳ አስተዳደር ወደ ሌላው መጠቅለል አስፈላጊ ከሆነ፣ ብዙ መለኪያዎች መጠናት ይኖርባቸዋል።

የወረዳው ወሰኖች ሽለቆዎች፣ ተራሮች፣ ወንዞች እና ረቀታቸው ይሆናል። የነዚህ ጉዳት እና ጥቅሙ ተመዛዝኖ በሚያመቸው መንገድ ሊስተካከል ይችላል። የዚህ ሁኔታ የገጠማቸው ወረዳዎች በጣም ጥቂት ናቸው ተብሎ የሚገመት ነው። አውራጃዎች የፈጠሩት ጠቅላይ አስተዳደር/እስቴት በመባል የሀገሪቱ ዋና አስተዳደር አካሎች ይሆናሉ። በወረዳው፣ አውራጃው እና ጠቅላይ አስተዳደር ውስጥ ያለው ኗሪ ሕዝብ፣ ባለሥልጣኖችን እንደ ከንቲባ፣ አገረገዥ፣ አቃቤህግ እና ሌሎችንም በህዝብ መመረጥ የሚገባቸውን ባለሥልጣናት፣ የፓርላማ እንደራሴ እና የሀገሪቱን መሪ በቀጥታ ወይም በእንደራሲወቻቸው አማካይነት ይመርጣሉ።

## ክፍል ስድስት

### የፖለቲካ መደቦች

የምስራቁ አህጉር፣ ኮሚኒዝም እና ሶሺያሊዝም ስረዐቶች ተሞክረው ለኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ ፍልስፍና እና ዕምነቶች ጋር ሳይጣጣሙ እና ሳይዋኸዱ ቀርተዋል። ጥፋትን ዳርገው፣ ትውልድን አውደመው አለፉ እንጂ ዘላቂ ጥቅም አልተገኘባቸውም። ኢትዮጵያኖች ከተፈጥሮ አስተሳሰባቸው ጋር በቀላሉ ሊያዋኺዱት የሚችሉት እና የሚያስንቅ ፍልስፍና ለከፍተኛ ዕድገት እና ብልጽግና አመች ሰርዐት በዚህ ዕቅድ የቀረበው ነው የሚል እምነት አለ። የምዕራብ ሀገሮች ለረጂም ጊዜ የተጓዙበት የካፒታሊዝም ስርዓት አበልጽጎ አሳድጓቸዋል። የሕዝቦቹ ስልጣኔ እጅግ የላቀ ነው። ዲሞክራሲ በጣም በስሎ ቢታይም፣ ሰላም የሚጠበቀው ጥቅጥቅ ባለ የቁጥጥር ኃይል ነው። የመላው ሕዝብ ብልጽግና ግን፣ በጭልፋ እየተለካ የሚዳረስ ይመስላል። የዲሞክራሲ ዕኩልነት የማይነጻጸር ሆኗል። ዕድገት ለዝቅተኛው ዜጋ፣ ጭላንጭል ሆኖ ቢታይም፣ ዕድገት ተብሏል በሌላ አንጻር። የአለሙ ጥቁር አፍሪካ ከሚገኘው ሕዝብ መሻሻል የተነጻጸረበት አስነዋሪ ሁኔታም ነበር። የዕኩልነት መለኪያ የሆኑት መስፈሪያዎች ግን፣ ከማደግ ይልቅ ቁልቁልነትን ያሳያሉ። የእኩል መብቶች ለጥቁሮች እና ሴቶች ለሌሎችም ያለው ልዩነት ሰፋ እንጂ ጠበበ አልተባለም። አሁንም እንደ ገምጋሚው አይን ነውና ብልጽግናው በሌላ መነጸር ሲታይ፣ በአስደሳች ሁኔታ ሀብታሙ እየመጠቀ ሲሄድ፣ ድሃው በአሳዛኝ ሁኔታ እየተንፈራፈረ ይገኛል። የምዕራቡ ችግር ግልጽ ብሎ፣ ነጭ የነጭ-ነጭ እና ነጭ ያልሆነ በመባል ተለይቶ ይታወቃል። አይንም መዝገብም ይለየዋል። አንዱ ሌላውን ለይቶ ያውቃል ማለት ነው። ኢትዮጵያውያን አንዱን ከሌላው ለይተው አያውቁም። ተቀናቃኝ የሚሉትን አጉልቶ በሚያሳይ መነጸር መፈለግ እና መመራመር አለባቸው። ማንነትን ለማወቅ ያስፈለገው ለመተማመን ብቻ ነው። ይህ መጥፎ ባህሪ መስሎ ቢታይም ባንጻሩ ይሻላል። ችግሩ እያደር ይጠፋል። ብዙ ግለሰቦች፣ ታላቁ የኢትዮጵያ መሪ፣ የኖቤል ሽልማት እጩ ጠ/ም ዶ/ር አቢይ አህመድ፣ ኦሮሞ ወይስ አማራ፤ ክርስቲያን ወይስ እስላም መሆኑን እና አለመሆኑን ለማወቅ ምርምር አድርገዋል። ጠርጣሪው ግለሰብ አቢይ ነጻነት የሰጠው ቢሆንም በዚህ የተጨነቀ ይመስላል። ም/ጠ/ም መኮንን ደመቀም ኢትዮጵያን ለሚመራው ያመቻቸ ቢሆንም፣ እንዲሁ ማንነቱ ተመርምሯል።

በብዙ መከራ ያለፈ ሰው መባበን ይበዛበታል። ከዚህ የባሱም አሉ። በክፍለ ግዛት የሚኖሩ፣ ሁለተኛ መንግሥት ፈጥረዋል። ከላይ ያላው ተደምሯል። አስገራሚው እና ታሪካዊው ሁኔታ፣ መሐል ያለው ከላይ የነበረው እንዲመለስ መሸጋገሪያ ድልድይ የመሆኑ ምክንያት ነው። ታሪክ ራሱን ደገመ!

በአንዳንድ ሀገሮች የዲሞክራቲክ እና የሪፐብሊካን ፓርቲ አካሎች ስለ ዲሞክራሲ አሰራራቸው 'የጠላ ቅራሪ' ሆነዋል። ያገሪቱን ማናቸውም ከባድ ችግር በዲሞክራቲክ አሰራር መሰረት እንዲፈቱ ተጠብቆ ሳለ፣ የዲሞክራሲው ስርዐት ስለአረዳቸው ተፋጠዋል። መፋጠጡ በአፍሪካ ምድር ቢሆን ኖሮ፣ ችግሩ በሮምታ ቶሎ አልቆ ነበር። በኢትዮጵያ ይህን መሳይ ጉዳይ ሊፈጥር የሚችለው የጎሳ ትርምስ ነው። ኢትዮጵያ ከምዕራቡ ዲሞክራሲ የላቀ ስርዐት ያስፈልጋታል። በኢትዮጵያ አንድን ጎሳ ብቻ የያዘ ወረዳ የለም። ማናቸውም ወረዳ የመንግስት ሰራተኛ፣ ጸሐፊ፣ ዳኛ፣ አስተማሪ፣ ኃኪም፣ ሰላም ጠባቂ፣ ነጋዴ፣ ወዘተ የሚኖርበት ግዛት ነው። ኢትዮጵያ በጎሳዎች በምድሯ ሁሉ የምታንሸባርቅ ዥንጉርጉር በመሆኗ አምላክ በነብር ይመስላታል። ይህን ተፈጥሮ የምዕራቡ ሕዝብ ያመልክበታል። በየከተማው ተመሳሳይ ገጾች "ትንሿ ኢትዮጵያ" የሚሉት እንዲስፋፋ ይሻሉ። በኢትዮጵያ እንዳይኖር የሚጥሩ አሉ።

## ክፍል ሰባት

## አዲስ የኢትዮጵያ ፖለቲካ መደቦች

**የአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ፖለቲካ መደቦች**

የኢትዮጵያ ፖለቲካ መደቦች(ፓርቲዎች)በሶስቱ ቀለማት ተመድበዋል። የፖለቲካ መደቦቹም፣ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ፖለቲካ መደብ (ፓርቲ) ተብለው ይጠራሉ። ከዚህ በታች፣ የየአንዳንዱ መደብ ፍልስፍና እና አቋም ባጫጭሩ ይገለጻል። ጠልቆ በመግባት ሁሉን ለመዘርዘር ለዚህ ዕቅድ አስፈላጊ ሆኖ አይታይም።

እያንዳንዱ የፖለቲካ መደብ በሚያምንበት ከሶስቱ የፍልስፍና መደቦች አንዱን በመምረጥ በሚደረገው ውድድር ምርጫ ለመመረጥ ይመዘገባል። የሚመርጠው ዜጋ፣ የሶስቱን ፖለቲካ አላማ ልዩነት እንዲያውቅና አቋማቸውንም ጠልቆ እንዲረዳ ማድረግ የፖለቲካ መደቦች ቅድመ ምግባራቸው ይሆናል። በዚህ መሰረት እያንዳንዳቸው የሚያራምዱትን ፍልስፍና አቋም ማስተማርና ማስረዳት ይኖርባቸዋል። ሶስቱም የፖለቲካ መደቦች በፈለጉት ወረዳ፣ አውራጃ ወይም ጠቅላይ አስተዳደር/እስቴት ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ። ጽ/ቤትም በፈለጉት ከተማ ማቋቋም ይችላሉ።

## የአረንጓዴ ፖለቲካ መደብ

የፖለቲካ መደቦች ሕዝብን በተለየ የአስተዳደር ችሎታቸው ለማበልጸግና ሰላምን ለማስፈን ያላቸውን ርዐይ ያቀርባሉ። የአረንጓዴው መደብ የሚያንጸባርቀው የፖለቲካ ፍልስፍና ተፈጥሮን እና የተፈጥሮን ጥቅም በጥንቃቄ ለማልማት የሚያሳስብ እና የሚያስተባብር የፖለቲካ መስክ

ነው። ይህንን የሚያሰምር ውስጠ-ህግ እና መመሪያ እንዲወጣ ይወሰውሳል። የአረንጓዴው ዋናው ፍልስፍና በእርሻ እና እርሻ-ነክ በሆኑ ልማቶች የሚያተኩር ይሆናል። የደን ዕርባታ፣ በምድር ውስጥ እና ውጭ ያሉ ፈሳሽ ወንዞች ልማትና አጠቃቀም፣ በምድር ውስጥና ላይ የሚገኙት ሀይቆች ልማት እና ጥቅምን ማጎልበት፣ የአሳ ርባታ ልማት በወንዞች እና ሀይቆች ማስፋፋት፣ የእንስሳ ጥበቃን፤ ዛፎች እና ሳር ቅጠሎች ምድርን እንዲያለብሱ፣ የደን ጥበቃ ለምድር እና ለአየር ጠባይ መናወጥ ወሳኝ ስለሆነ ያንን ባማያፈርስ መንገድ ልማት እንዲካሄድ መልካም ዕቅድ በስራ እንዲውል፣ ኢትዮጵያ እራሷን በእርሻ ምርቶች መግባ፣ ለውጭ አለም ጥሬ እና ፍራፍሬ ለሽያጭ እንድታቀርብ ብቁ እንድትሆን ማድረግ፣ እነህን እና ተመሳሳይ ልማቶችን ለማስፋፋት፣ የአረንጓዴ ፓርቲ መሪዎች ጠቃሚ ፖሊሲዎች እንዲወጡ ያደርጋል።

በመጀመሪያው ምርጫ ወቅት ይህ አዲስ ስርዓት ውዝግብ ሊፈጥር ስለሚችል፣ መንግሥትና የፖለቲካ መደቦች መራጩን ሰው ስለ ፍልስፍናው ለማስተማር ሰፊ ጊዜ እና ፕሮግራም ተመድቦ ትምህርት እንዲሰጥ ይደረጋል። ትምህርቶቹ በሬድዮ፣ ቲቪ እና ጋዜጣ አማካይነት የሚሰጡ ሲሆን፣ በተጨማሪ በት/ቤቶች፣ በአደባባዮች እና በሚያመቹ መስኮች ሁሉ ውይይትና ገለጻ በሰፊው እንዲካሄድ ይደረጋል። ይህ ትምህርት በምርጫ ቦርድ አማካይነት እንዲሰጥ ይደረጋል። በዚህ መሰረት ከየወረዳዎች የሚመረጡት አውራጃውን ወክለው፣ የአውራጃው ተመራጮች ክፍለግዛቱን በመወከል የሀገሪቱ እንደራሴዎችና መሪ ይመረጣሉ። ይህ ስርዐት ለየት ባል መልክ ሊካሄድ ይችላል።

### የቢጫ ፖለቲካ መደብ (ፓርቲ)

የቢጫ ፖለቲካ መደብ ፍልስፍና ስለ ሕዝባዊ እድገት ግንባታ እና ብልጽግና የሚያስፈልጉትን መሰረታዊ ልማቶች የሚያንጸባርቅ የፖለቲካ መደብ ይሆናል። የቢጫው መደብ ፖለቲካ ፍልስፍና የሕዝብን ሰላም እና የዜጋ መብቶች ላይ የሚያተኩር ይሆናል። በመንደር፣ በትንሽ እና ትልቅ ከተማ የሚኖሩትን ዜጎች ሁሉ፣ የት/ቤት፣ የሕክምና ጣቢያዎች፣ የውሃ ማደያ፣ የመብራት እና ተመሳሳይ አገልግሎቶች እንዲያገኙ፣ ከመንግሥት ጥቅም እንዳይነፈጉ እና ወደ ኋላ እንዳይቀሩ ያደርጋል። በትላልቅ ከተሞች የሚኖረው ሕዝብ በተጨናነቀ አኗኗር ምክንያት ጤናው እንዳይታወክ፣ በንጽሕና ጉድለት በሽታ እንዳይራባ፣ መቆጣጠሪይ ድርጊቶች እንዲቋቋሙ ፖሊሲ እንዲወጣ የቢጫ ፖለቲካ መደብ ይጥራል። የቢጫው ፖለቲካ መደብ ሚና በጣም ሰፊ ነው። የሕዝብን ኑሮ እና ደህንነት በሚመለከት፣ በተለይም በከተማ አያሌ ሕዝብ በሚኖርበት ውስጥ ተጓድለው የሚገኙትን አገልግሎቶች እንዲሻሻሉ፣ የከተማ መንገዶች በዛፍ ቅጠል እና በአበባ እንዲያንሸባርቁ ኗሪው የተሻለ ኑሮ እንዲኖር ማድረግ የቢጫ ፓርቲ መደብ ዋናው ሚናው ይሆናል። ከተሞች የብዙ የተለያዩ ጎሳወች መኖርያ ስለሆኑ፣ የተለያዩ ባህሎችን እና የሀገር ቅርሶች ከተማወችን ውበት የሚሰጡና የሚያደምቁ ስለሆነ፣ የቢጫ ፓርቲ መደብ እነህ ውበቶች እንዲያድጉ ያደርጋል። ማናቸውም ዜጋ በዕድሜው፣ ጾታው፣ ባህሉ እና

በማናቸውም እንከን በዝቅተኝነት እንዳይታዩ እና አገልግሎቶቹ እንዳይጓደሉባቸው የቢጫው ፓርቲ ለመብታቸው ይቆማል። ማንም ሰው በሽማግሌነቱ፣ ሴት ወይም ሕጻን በመሆኑ በማናቸው ዕክል ለርሀብ እንዳይጋለጥ እና አደጋ እንዳይደርስበት የቢጫው ፓርቲ መደብ ይህንን ችግር የሚከላከልበት በሕዝብ እና መንግሥት ተቋሞች የዕርዳታ ማዕከሎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል።

የቢጫው ፓርቲ መደብ ባለፉት አርባ አመታት በግለሰቦች የደረሰ አሰቃቂ ችግር አሁንም ብዙ ግለሰብ እና ቤተሰብ ኑሮው የተጨናገለ ሆኖ ስለሚገኝ፣ ለነዚህ ብስቁል ሰወች ዕርዳታ እንዲያገኙ የቢጫ ፖለቲካ መደብ ዕርዳታ እንዲያገኙ ያደርጋል። ዕርዳታው እንዲስፋፋ፣ ከውስጥ እና ከውጭ የበጎ ድርጅቶች ልገሳ እንዲያደርጉ የቢጫ ፓርቲ ትብብር ያረጋል።

## የቀይ ፖለቲካ መደብ/ፓርቲ

የቀይ ፖለቲካ መደብ ፍልስፍና በንግድ፣ ኢንዱስትሪዎችና በሀገር ደህንነት ላይ የሚያተኩር እና ለነዚህ ልማቶች የሚቆም ድምጽ ይሆናል። ንግዶች እንዲስፋፉ፣ ከውጬ አለም ጋር ያሉት ንግዶች እንዲጠናከሩ፣ ያገሪቱ ምርቶች ጥቅማቸው ጎልቶ እንዲታይ እና የገበሬዎች እና ነጋዴዎች ጥቅም ከፍ እንዲል መመሪያወችን ያዘጋጃል። የአምራቹ ገበሬ፣ አዘጋጁ ኢንዱስትሪ፣ አቀባባዩ ነጋዴ፥ የተገልጋዩ ሕዝብ ጥቅሞች የተዛቡ እንዳይሆኑ ቁጥጥር እንዲደረግ መመሪያ ያወጣል።

አፍሪካ ከኮለንያሊዝም ስርዐት ወጥቶ አሁን የምዕራቡ እና የምስራቁ "ግሎባላይዜሽን" በተባለው መርህ፣ ፕ/ር መስፍን 'ሙኋለም' በማልት የሰየሙት፣ እኔ ደግሞ በድፍረት 'አለምታዊ' ያልኩት ስርዐት የአለም ድሃ ሀገር ነጋዴዎችና እና የምዕራቡ ከበርቴዎች በንግድ የጋራ ጥቅም ማካሄጃ አለምታዊ ስርዐት ዘርግተዋል። ከበርቴዎች በገንዘብ ኃይል እና በቴክኒዎሎጂ ጥበብ የተደገፉ ስለሆኑ፣ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አስተናጋጅ አገሮች ደግሞ የሰው ኃይል እና ማዕድኖች፣ የእርሻ ኃብቶች በአለምታዊው ንግድ ተፈላጊ አድርጓቸዋል። ሆኖም፣ የውጬ አለም እጅግ የረቀቀ ህጋዊ አሰራር ስለሚከተል፣ በአለምታዊው ስርዐት በሰፊው ሊጠቀም ችሏል። እንደኢትዮጵያ ያለው አስተናጋጁ ሀገር ግን፣ በአሰራር ስልት እጥረት፣ በ'ብርዮክራሲ' እና ሙስና ምክንያት ሰፊው ጥቅሙ እንደተጓደለበት ይታወቃል። የቀይ ፖለቲካ መደብ መሪዎች በአለምታዊው ንግዶች ፖለሲ ዙሪያ የተዛቡት አሰራሮች እንዲስተካከሉ፣ ቁጥጥሮች እንዲደረጉ አስፈላጊ ፖሊሲዎች እየነደፈ በስራ እንዲውሉ ያረጋል።

የቀይ ፖለቲካ መደብ በኢንዱስትሪዎች፣ ንግዶች፣ ማዕድኖች መስፋፋት የሀገር ዕድገት ዕቅዶች ላይ መመሪያ ያዘጋጃል። የቀይ ፖለቲካ ፓርቲ ከዚህ ምግባር ጋር የተያያዙ ሌሎች ጉዳዮችን አስመልክቶ መመሪያ እያወጣ፣ የሀገሪቱ ጥቅም እንዲዳብር መመሪያና አስፈላጊ ህጎች እንዲደነገጉ ያደርጋል። የቀይ ፖለቲካ መደብ በተጠቀሱት መርህ ግብሮች ብቻ ሳይወሰን፣ በሳይንስ እና በቴክኖሎጂ በሚያስፈልገው እርምጃ ሁሉ ኢትዮጵያን በሚያሳድጉ እና በሚያስነቁ መስኮች መመሪያ አቋሞችን ይፈጥራል። ኢትዮጵያ በውጬ አለም ያላትን መልካም ግጽና በጎ አቋም በመስረጽ መመሪያ ያወጣል።

## የፌደሬሽን አወቃቀር

የኢትዮጵያ አስተዳደር በጎሳ ላይ የተመሰረተ ፌደራል አወቃቀር ስለነበረ፣ የኢትዮጵያ መጥፊያ እንጂ መልሚያና ማደጊያ ስላልነበረ፣ መደምሰሱ የማይቀር ነበር። በምትኩ አዲስ አወቃቀር እንደሚያስፈልግ ግልጽ በመሆኑ፣ የዚህ ዕቅድ መጠንሰስ ምክንያቱ ይኼው ነው። ጠ/ም ዶ/ር አብይ እና በጎኑ ያሉት ዕንቁ መሪዎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአለም ፊት ኢትዮጵያን ለመገንባት ቃል ገብተዋል። "ኢትዮጵያ አትፈርስም!" ኢትዮጵያ ካለችበት ችግር እናሸጋግራታለን በማለት ያስተጋቡት ተስፋ የማይታጠፍ ነው። ያገኙት ድጋፍ ወደር የሌለው ሆኗል። የነጋበት "የቀን ጅብ" ከእንግዲህ ወዲህ ለኢትዮጵያ አስጊ አይሆንም። ኢትዮጵያ ከአለሙ የፌደራል አስተዳደር ማሕበር አባልነት ራሷን ማግለል ይኖርባታል። በጎሳ እና በቋንቋ የተደራጀው ፌደራል ስርዐት ኢትዮጵያን አይወክልም። ኢትዮጵያ በወራሪ ኃይል ሳይሆን፣ ሕዝቧ በሚመርጠው መልካም አስተዳዳር እና ግዛታዊ ፌደራላዊ አወቃቀር ስትካተት፣ ከድርጅቱ አባልነት ትመዘገባለች።

የኢትዮጵያ ፌደራል አስተዳደር የሚገነባውና የሚዋቀረው በወረዳዎቹ ጀምሮ ይሆናል። ይህ አወቃቀር ተፈጥሮአዊ ያረገዋል። ወረዳዎች በሞላ ጎደል አራሽ ገበሬ የሚኖርባቸው ቢሆኑም፣ ገጻቸው እየተለወጠ ነው። የስልጣኔም አኗኗር እየደረሳቸው ነው። አሁንም ተፈጥሮ በሚያግዘው መሰረት፣ የወረዳወች የምድር አቀማመጥ፣ በወንዞች፣ ተራሮች፣ ሸለቆች፣ ሜዳዎችና ኮረብታዎች የሚወሰን ስለሆነ፣ በዚሁ ተፈጥሮ አቀማመጥ መሰረት የአስተዳደሩ ወሰን ተቀርጿል። ይህ ለሕዝቡ እድገት አመች ወይም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ያንድ ወረዳ ህዝብ ከማናቸውም አውራጃ አስተዳደር ውስጥ ቢዋቀር፣ ለኗሪው የሚበጅ ከሆነ ማስተካከል ተገቢ ይሆናል። ይህም ማለት፣ ወረዳውን ከላይ በተጠቀሱት ተፈጥሮዎች አቀማመጥ እድገቱ የሚደናፈቅ ከሆነ ከሚቀርበው አውራጃ ማቀላቀል የሁሉ ጥቅም የሚሰጥበት አደረጃጀት በጎ ሆኖ መታየት አለበት።

በዚህ መሰረት ወረዳዎች፣ አውራጃዎች እና ክፍለግዛት ወይም የፌዴራል ስቴት የሚባሉ የአስተዳደር ቅርጽ ይይዛሉ። ለምሳሌ፣ የወሎ ክፍለግዛት አስተዳደር ወይም የወሎ ፈደራል እስቴት የሚባል ይሆናል። ሌሎቹም በዚህ መልክ ይጠራሉ። በዚህ ፌደራል አስተዳደር አወቃቀር መልክ የምትቋቋም ኢትዮጵያ፣ ዕድገቷን የሚያደናቅፍ ሀሳብ ሊኖር አይችልም። ዳሩ ግን፣ የሰው ባህሪ ሆኖ፣ አንዳንዱ ግለሰብ በዚህ ሂደት ጉዳት ሳይኖር ጉዳት ይታየዋል። ጥቅሙ የራሱ ብቻ አለመሆኑ የሚያስፈረግጠው ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ዳሩ ግን፣ ሰው እያደር የሚሻሻል ስለሆነ፣ በሀሳቡ ጸንቶ አይገኝም። የለውጥ ኃይል ያይልበትና ይለወጣል። ከላይ የተገለጸው ስልት ኢትዮጵያ "የዜጋ/የግለሰብ ሀገር" የምትባል ያረጋታል። ግለሰብ ይነግሳል፣ የጎሳ ጥቅም ሚና የሚያሳፍር ሆኖ ይታያል፣ በቅጽበት ተረትና ታሪክ ይሆናል። ይህ ሲጠናቀቅ፣ የኢትዮጵያኖች ተስፋ እና ምኞች ተሟላ ይባላል።

## የኤርትርያ ጉዳይ

ይህ ዕቅድ ኤርትራን እንደ አንዱ ዋና የኢትዮጵያ ክፍለግዛት ተሳታፊ አድርጎ በመውሰድና በመደመር የተጸነሰሰ ዕቅድ ነው። እንኳን የወደፊቱ አሁንም ላለው የኢትዮጵያ የውስጥ ችግር ሲታይ፣ ኤርትራ አንደ ደገን ሆና እንደቀረበች የሚያመለክቱ ቁምነገሮች አሉ። ይህ መሆኑ ሌላ ትርጉም ሳይሰጠው የመሪዎች ብልሀትና ጥበብ ያመጣው ራዕይ ሆኖ መታየት አለበት። ኤርትራ በብዙ አንጻር ይገባት የነበረውን ማዕከል በታሪክ አጋጣሚ አገኝታለች። በዚህ ቦታዋ መመለሷ ተአምር ሳይሆን፣ የነበረው ስርዐት ጊዜውን ሲጨርስ፣ ኤርትራም የነበረችበትን ችግር ተላቃ ወደ መልካሙ ጎዳና ተመለሰች ብሎ ማሰብ ተገቢ ነው። ይህ ሲባል፣ ኢትዮጵያ ከፍ ማለቷ፣ ኤርትራም እንዲሁ መሆኗን የሚያመለክት ነው። ኤርትራ ከናት ሀገሯ በማናቸውም መልክ መቀላቀሏ ለኢትዮጵያና ኤርትራ ሰው ያፈለቀው ደስታ ታሪካዊ እና ዘላለማዊ ሆኖ እና መስሎ ታይቷል። ይህ እንዳይቀለበስ፣ ማንም ኢትዮጵያዊና ኤርትራዊ የሚሰዋበት እንደሆነ ያለው ግባት ያሳያል። ከዚህ በኋላ፣ የኤርትራ ችግር የኢትዮጵያ፣ የኢትዮጵያ ችግር የኤርትራ እንደሚሆን የማያጠራጥር ነው።

የሁለቱ መሪዎች ወዳጅነት እና የሁለቱ ሀገሮች ሕዝብ ወዳጅነት ደምቆ ታይቷል። ፕ/ኢሳዒያስ፣ ኤርትራ እና ኢትዮጵያ በኮንፈደሬሽን ይቀላቀሉ ብሎ የሰነዘረው ሕልም ተፈጸመለት ማለት ነው። ኢትዮጵያ ከኤርትራ ጋር የምትውሃደበት ስርዓት፣ አንዱ ሲጎዳ፣ ሁለቱም እንደሚጎዱ፣ አንዱ ሲበለጽግ፣ ሁለቱም እንደሚበለጽጉ በሚያደርጋቸው የዲሞክራታዊ አስተዳደር እስስር ነው። ይህ ዕቅድ በዚህ ልቦና ከተዘረጋ፣ ምናልባት ሁለቱም ሕዝቦችና መሪዎች በዓለም ታይቶ የማይታወቅ ታሪካዊ ስራ የሚፈጽሙ ይሆናል። ከዚህ የተለየና የበለጠ ወዳጅነት በምንም ዘመን አይገነባም። ጠ/ም ዶ/ር አቢይ ምናልባት ሊተካ የማይችል መሪ ስለሆነ፣ ኢሳዒያስም ብዙ ዘመን ስለሌለው፣ ይህ ወቅት የታሪኩ ዕንቁ ፍጻሜ እንዲሆን የሁለቱን መሪዎች ጥበብና አርቆ የማሰብ ችሎታ ይጠይቃል። ትተውት የሚሄዱትን ዘመን ያዩታል። የሚኮሩበት ነው። ከዚህ የበለጠ የሕይወት ጸጋ ማንም ጀግና የሚመኘው አይኖርም።

## መደምደሚያ

ብዙ አጸያፊ ስህተት በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተፈጽሟል። ያ-ታሪክ ለማስታወሻ ደብተር ተዳርጓል። ከዳር እስከዳር ያለው የኢትዮጵያ ሰፊ ቅርስ እና ኃብትን ለመጠቀም አዲስ ባህሪን እና አዲስ ፍልስፍናን መጎናጸፍ ያስፈልጋል። ያለንበት አለምታዊ ሁኔታ ካለፈው ዘመን እጅግ ልዩ ነው። የአለምታዊውን ግስጋሴ ለመቋቋም እና አብሮ ለመጓዝ የሕዝባዊ፣ ብልጽግና እና አስተዳደር አቋማችንን ማስተካከል ያስፈልጋል። ሰፊው ዕድገት የምስራቅ አፍሪካ ሀገር ሕዝቦችን፣ ከዚያም ከቀረው አፍሪካ ሕዝብ ጋር በብዙ ጥቅም መተሳሰር ሊታሰብ ይገባል። በነዚያ አቅጣጫ ያለው ዕድገት እንዲወጠን፣ መጀመሪያ፣ ራስን ማዘጋጀት ያስፈልጋል። በኢትዮጵያና ኤርትራ በኩል ያለው ውኽደት እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ እርምጃ ነው። መጀመሪያ

መታመን ያለብት ጉዳይ፣ ኢትዮጵያ ካላደገች፣ ኤርትራ እንደማታድግ ነው። ኤርትራ ሰላም ካልተጎናጸፈች፣ ኢትዮጵያ ዕረፍት እንደማይኖራት መረዳት ያስፈልጋል። ኢርትራ ከኢትዮጵያ ጋር በፌደራሳዊ ስርዐት አወቃቀር ብትጣመር፣ ችግሯን ሁሉ ኢትዮጵያ በቀጥታ ትጋራለች። ይህ መታወቅ እና ከማንም ህልውና ጠልቆ መግባት አለበት።

የውጩ የፖለቲካ ስልት ለኢትዮጵያ የሚመች አይደለም፣ አይሆንም። ስለዚህ፣ የአለሙን ስርዐት መቅዳት አያስፈልጋትም። የፋሸሸትን "ከፋፍለህ ግዛ" ፍልስፍና ወያኔዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት እንዲሰፍን አደረጉ። ባደረባቸው ተንኮል እና የኃብት መጠማት፣ ኢትዮጵያ ከገባችበት አትወጣውም ብሎ በማሰብ፣ በ"ጎሳ ፌደራል አስተዳደር" ሸለቆ ውስጥ አስገቧት። ይህን ብልሽት እንደ ጥቅም በመቁጠር እንዲቀጥል የሚያራግቡ ግለሰቦች አይጠፉም። ይህ ጸሐፊ ህሊናቸውን በመንካት እንዲያስቡ እና እንዲቀለበሱ አደርጋለሁ በሚል ዕምነት የሚሰነዝረው አንድም ሀሳብ የለውም። የልባቸውን እና ይህሊናቸውን ጠጠርነት በሚገባ ይረዳል። የኢትዮጵያ መሪዎች እና ሕዝብ የሚጠብቀውን ከባድ ስራ ማስተጋባት ጠቃሚ ነው። የተበላሸውን ለመጠገን አያሌ ጉልበት እና ትዕግስት ይጠይቃል። በዚህ ዕቅድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቁን ሽግግር እንደሚፈጽም የማያጠራጥር ነው።

ወረዳዎች ለኢትዮጵያ ሰላም እና ዕድገት መሰረትና ምሰሶ ናቸው። በነሱ መቀጣጠል ሰፋፊው አስተዳደር ይዘረጋል። ኢትዮጵያ ሰፊ ሀገር ስለሆነች፣ የምድር ቅርጿም የተለያየ በመሆኑ፣ ተመጣጣኝ ልማት ለማዳረስ አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል። ይህንን በመገንዘብ ልዩ ስልቶችን መጠቀም ያስፈልጋል።

በአረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ አርማ የሚመደቡት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሌሎች ሀገሮች ከሚጠቀሙበት ኮምኒዝም፣ ሶሺያሊዝም፣ የዲሞክራቲክ/ሪፐብሊክ ከሚባሉት የአስተዳደር አወቃቀር ፍልስፍናዎች ለየት ያሉ ናቸው። ስለሆነም፣ ከውጩ የሚወረሱ ችግሮች አይኖሩም። በዚይ አማካይነት የሚመጡት ተጽእኖችም እጅግ ያንሳሉ። አዲሱ አወቃቀር የሚከላከል እና የሚቋቋመው ይሆናል። ይህ እጅግ ጠቃሚ ስትራትጂ ነው። ዕቅዱን አጥብቀው ሲያሰላስሉት ውበቱ ቁልጭ ብሎ ይታያል።

ማሳሰቢያ

ስለ ዕቅዱ በማንኛውም መድረክ ለመወያየት እና ፍልስፍናውን ለመግለጽ፣ ጥያቄዎችን ለመመለስ ደራሲው ፈቃደኛ ነው። አስተያየት እንዲላክለት ይጓጓል።

ጸሐፊውን ለማገኘት፥ zegfantam@aol.com or zegfanta57@gmail.com